# የጥንት የጠኋቱ

ገና በማለዳ ፣ ራዕይ ሰንቆ
ላገሩ ደህንነት ፣ የተለመ አርቆ
ለረጅሙ ትግል ፣ ቆርጦ ፣ ባጭር ታጥቆ
በዱር በከተማ ፣ ከፋሽስት ተናንቆ
ደሙን ያፈሰሰ ፣ ለናት አገር ወድቆ
የጓዱን አደራ ፣ ቃልኪዳን ጠብቆ
ዛሬም ይታገላል ፣ ማቸነፉን አውቆ ።

ዛሬም ይፋለማል ፣ ከጎጠኞች ጋራ
ፊትአውራሪ ሆኖ ፣ ትግሉ እንዲጎመራ
ህብረ ብሄራዊ ፣ ብርሃን እያበራ
የአንድነት ሰብል ፣ ዘሩን እየዘራ
ህዝብ እያስተማረ ፣ ትግሉን እያጠራ ።

የቀድሞ የጥንቱ ፣ ባለ ብሩህ ፋና
የማያወላዳው ፣ በያዘው ጎዳና
ትላንትና ዛሬም ፣ ባለማው የጸና
ታሪክን የሰራ ፣ ያለው አኩሪ ዝና
ኢሕአፓ ነው ዛሬም ፣ ልበ ሙሉ ጀግና ።

አታጋይ ኢሕአፓ ፣ የጥንት የጠኋቱ
ኮስታራ ኮምጣጣ ፣ የመረረ ሀሞቱ
ኢትዮጵያዊነቱ ፣ የሚታይ በፊቱ
የማይንበረከክ ፣ የብርቱዎች ብርቱ
ኢሕአፓ መፍትሄው ፣ ትንታጉና እሳቱ ።

ከትውልድ ትውልድ ፣ የኖረው ታፍኖ
በድል አድራጊነት ፣ ትግሉ ተከናውኖ
አገር ተረጋግቶ ፣ ሳይኖረው ተፅእኖ
የጎጠኞች ስርአት ፣ ፈርሶ ተበትኖ
ሰላም ትነግሳለች ፣ ስልጣን የህዝብ ሆኖ ።

ታዛቢ.ው

February, 14, 2010